# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ

# እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

## የጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃ ሽግግር አፈፃፀም

## መመሪያ ቁጥር 117/2014

## መግቢያ

በከተማችን ውስጥ የሚገኙ ስራ ፈላጊ ነዋሪዎችን በመለየት አስፈላጊውን ስልጠና ማመቻቸት፣ ማደራጀት፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የመስሪያ ቦታ እና የገበያ ትስስር ድጋፎች እንዲያገኙ በማድረግ ሰፊ የስራ ዕድል እንዲፈጠር እና በሃገራችን የሚታየውን ስራ አጥነትና ድህነት መቀነስ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞች እንደ የዕድገት ደረጃቸው ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰንና ሽግግር አፈጻጸም መመሪያ የተስተዋሉ ያልተመለሱና ያልተፈቱ ችግሮች ለመፍታትና ኢንተርፕራይዞችን ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል እንዲያገኙ ለማድረግ እና ግልጽነትና ተጠያቂነት ሥርዓት በማካተት ሥራውን መምራት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሠ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ “የጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ  እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃ ሽግግር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 117/2014” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **“ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ”** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት ፤የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ 5 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታል መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ እስከ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺ/ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ እስከ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺ/ ድረስ የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
2. **“አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ”** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታል መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001.00 /ሃምሳ ሺ አንድ/ እስከ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺ /ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001.00 /አንድ መቶ ሺህ አንድ/ እስከ ብር 1,500,000.00/ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ/ ድረስ ያለ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
3. **“መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ31 እስከ 100 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ካፒታል መጠኑ ህንጻን ሳይጨምር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከብር 1,500,001.00 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ / እስከ ብር 20,000,000.00 (ብር እስከ ሃያ ሚሊዮን ብር) እና በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 500,000.00 / አምስት መቶ ሺህ ብር /እስከ ብር 20,000,000.00 (ሃያ ሚሊዮን ብር) ያለ ኢንተርፕራይዝ ነው፤

4. **“ከፍተኛ ኢንዱስትሪ”** ማለት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ 101 በላይ ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ31 በላይ የሆነ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ31 ሰዎች በላይ ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ21 በላይ መሆን አለበት፤

5. **“የኢንተርፕራይዝ ዕድገት ደረጃ ሽግግር”** ማለት አንድ የኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃው የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃ የሽግግር መስፈርቶቹን በማሟላት መሸጋገር ሲችል ነው፤

6. **“የምሥረታ ወይም ጀማሪ ዕድገት ደረጃ ”** ማለት በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አውጥተው ወደ ስራ የተሰማሩና ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ነዋሪዎች የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ተግባር የሚጀምሩበት ነው፤

7. **“የታዳጊ ወይም መስፋፋት ደረጃ ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሲሆንና ትርፋማነቱ ቀጣይነት ሲኖረው ነው:: በዚህ ደረጃ ያለ ኢንተርፕራይዝ በምስረታ ደረጃ ከነበረው ቀጥሮ የሚያሠራው የሰው ኃይል ቁጥርና የጠቅላላ ሀብት መጠን ዕድገት ያለው ነው፤

8. **“የመብቃት ዕድገት ደረጃ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የገበያ ድርሻውን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በሥራ ላይ ካዋለና ለዘርፉ የተቀመጠውን ትርጓሜ መስፈርት ሲያሟላና ወደ ታዳጊ መካከለኛ ሲሸጋገር ወይም በአለበት ደረጃ ጥቃቅን፤ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ በመሆን በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን ነው፤

9. **“ቋሚ የሥራ ዕድል ”** ማለት በማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ውስጥ የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከአንድ ዓመት ያላነሰ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በደመወዝ ክፍያ ሰነድ የተረጋገጠ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ነው፤

10. **“ጊዜያዊ የሥራ ዕድል”** ማለት በማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ውስጥ ከአንድ ዓመት ያነሰ ጊዜ ክፍያ በማግኘት ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ነው፤

11. **"ነባር ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ህጋዊ ሰውነት ወይም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አግኝተው አንድ ዓመት እና በላይ የሞላቸው ኢንተርፕራይዝ ነው፤

12. **"አዲስ ኢንተርፕራይዝ "** ማለት በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አግኝቶ ወደ ሥራ ከተሰማራ አንድ ዓመት ያልሞላው ኢንተርፕራይዝ ነው፤

13. **"የገበያ ትስስር"** ማለት ለአንድ ኢንተርፕራይዝ የገበያ ዕድል መፍጠር ከመንግስት ተቋማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሀገር ውስጥና ውጪ ከሚገኙ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት በኀንዮሽና በተዋረድ ግንኙነት የሚፈጠር የግብይት ወይም የሥራ ትስስር ነው፤

14. **"ጠቅላላ ሃብት"** ማለት የአንድ ኢንተርፕራይዝ የተከፈለ እና በብድር የተገኘ ሃብት ነው፤

15. **"የተጣራ ካፒታል"** ማለት የአንድ ኢንተርፕራይዝ ጠቅላላ ሃብት ሲቀነስ ዕዳ ነው፤

16. **"የምርት ወይም የአገልግሎት ማስተዋወቂያ ዘዴዎች"** ማለት ምርትን ወይም አገልግሎትን በማስተዋወቅ የመገናኛ ብዙሃን ፤ንግድ ትርዒትና ባዛር፤ በራሪ ወረቀት፤ ቢዝነስ ካርድ፤ ቋሚ የማስታወቂያ ቦርድ ፤ ካታሎግ፤ ዳይሬክተሪ፣ የኢንተርፕራይዞችን ስም የያዙ ስጦታዎች እስኪሪቢቶ፣ ቁልፍ መያዣ፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ፖስት ካርድ ፣ እና ድረ-ገጽ ነው፤

17. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

18. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ቢሮው፣ በጽህፈት ቤቶች እና በጥቃቅን፤ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

4. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

የጥቃቅን ፤ አነስተኛ ፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃ ሽግግር አፈፃፀም የአሰራር ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆንና የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረጉ ድጋፎችን መስጠት ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰን እና ሽግግር

5. የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰን

1. በንግድ ህጉ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አውጥተው ኢንተርፕራይዙ የያዘውን የሰው ሃይልና የካፒታል መጠን መሰረት በማድረግ በተደራጀበት ስራ መስክ ተለይቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቃቅን ጀማሪ ወይም አነስተኛ ጀማሪ ወይም መካከለኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ መሰጠት አለበት፤
2. አንድ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅን ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የካፒታል መጠን ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺ/ ያልበለጠ እና የሰው ሃይል እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ እስከ 5 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፤
3. አንድ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅን ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በአገልግሎት ዘርፍ የካፒታል መጠን ብር 40,000.00 (አርባ ሺ) ያልበለጠ የሰው ሃይል እስከ 5 ሰው መሆን አለበት፤
4. አንድ ኢንተርፕራይዝ አነስተኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት በማግኘት በኢንደስትሪ ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 100,001.00 /አንድ መቶ ሺ አንድ/ ያላነሰ እና የሰው ሃይል እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ ከ 6 እስከ 30 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፤
5. አንድ ኢንተርፕራይዝ አነስተኛ ጀማሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በአገልግሎት ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 50,001.00 /ሃምሳ ሺ አንድ/ ያላነሰ እና የሰው ሃይል እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ ከ 6 እስከ 30 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፣
6. አንድ ኢንተርፕራይዝ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 1,500፣000.00 በላይ / አንድ ሚሊዮን አመስት መቶ ሺህ ብር/ እስከ 20,000,000.00 / ሃያ ሚሊዮን ብር / ያልበለጠ እና የሰው ሃይል እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ ከ 31 እስከ 100 ሰው የቀጠረ መሆን አለበት፤
7. አንድ ኢንተርፕራይዝ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ለማግኘት በአገልግሎት ዘርፍ የካፒታል መጠን ከብር 500,000.00 / አምስት መቶ ሺህ ብር / ያላነሰ እና የሰው ሃይል እራሱንና ቤተሰብን ጨምሮ በቋሚ 20 ሰው በጊዜያዊነት እስከ 15 ሰው የቀጠረ

መሆን አለበት፤

8. አንድ ኢንተርፕራይዝ ጥቃቅን ወይም አነስተኛ ወይም መካከለኛ የዕድገት ደረጃ ለማግኘት የሰው ሃይል ብዛትና የካፒታል መጠን የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ በካፒታል መጠን የሚወሰን መሆን አለበት፡፡

6. <u>የነባር ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ፤ እድሳትና የቆይታ ጊዜ</u>

1. አንድ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ማሳደስና ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ መሸጋገር የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት፤
2. ለኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እድሳትና ሽግግር የሚሰራው ከሐምሌ 1 እስከ ጥቅምት 30 ድረስ ብቻ ነው ፡፡ ይሁንና የዕድገት ደረጃውን መታደስ ባለበት ወቅት ከሐምሌ 1 እስከ ጥቅምት 30 ድረስ እድሳት ያላደረገ ኢንተርፕራይዝ፡-

   ሀ) ከህዳር 1 እስከ 30 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የዕድገት ደረጃው እንዲታደስ መደረግ አለበት፤

   ለ) በተሰጠው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ካላሳደሰ የዕድገት ደረጃው ተሰርዞ ከድጋፍ ማዕቀፎች ውጪ መደረግ አለበት፤

   ሐ) ለኢንተርፕራይዝ የሚሰጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በአካል መድረስ ያለበት ሲሆን የኢንተርፕራይዙ ባለቤቶችን በአካል ማግኘት ካልተቻለ በመስሪያ ቦታው ላይ መለጠፍ አለበት፡፡ ቋሚ የመስሪያ አድራሻ የሌለው ኢንተርፕራይዝ ከሆነ ህዝብ በሚያየው ቦታ እንዲሁም በወረዳው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ አለበት፤

   መ) ኢንተርፕራይዙ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አውጥቶ ወደ ስራ ከገባ 1 ዓመት ያልሞላው ከሆነ እንደማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ከሐምሌ 1 እስከ ጥቅምት 30 ድረስ ማደስ ያለበት ሆኖ በሰራው የሂሳብ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት መሰረት የደረሰበት የዕድገት ደረጃ መሰጠት አለበት፤

3. አንድ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግር የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ ከተገኘ በየትኛውም የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ኢንተርፕራይዝ በቀጣዩ ዓመት መስፈርቱን አሟልቶ ከተገኘ እርከኑን ሳይጠብቅ እስከ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ ማግኘት ይችላል፤

4. አንድ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ እድሳት የሚሰጠው ለደረጃው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ያሟላውን የዕድገት ደረጃ ዓይነት ሲሆን በያዘው የዕድገት ደረጃ የቀጠለ ወይም ዝቅ ያለ ከሆነ፡-

   ሀ) ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርተፊኬቱ እድሳት ተደርጎለት ለሚመለከተው ደጋፊ ባለሙያና ባለድርሻ አካላት በደብዳቤ በማሳወቅ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኝ መደረግ አለበት፤

   ለ) በተሰጠው ተጨማሪ ድጋፍ ከፍ ወደ አለ የዕድገት ደረጃ ያልተሸጋገረ ከሆነ ድጋፍ ከሰጠው አካል መረጃ በመሰብሰብና በማረጋገጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬቱ መታደስ አለበት፤

   ሐ) አምስተኛ ዓመት ላይ ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃውን ቢያሻሽልም ባያሻሽልም ወደ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ካልተሸጋገረ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬቱ ተሰርዞ የጥቃቅን ፤ አነስተኛ ፤ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃ ሽግግር ወይንም ዕድሳት አገልግሎት እንዲቋረጥ ይደረጋል፤

5. በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አውጥተው ስራ ላይ የሚገኙ ነባር ኢንተርፕራይዞች ከዚህ በፊት ምንም አይነት የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ያልተሰራላቸው ከሆነ እንዲሰራላቸው ሲደረግ በመስፈርቱ መሰረት ተመዝኖ በደረሱበት የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት መሰጠት አለበት፡፡ ይሁንና የተሰጠው የዕድገት ደረጃ የሚያገለግለው እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ብቻ መሆን አለበት፤

6. አንድ ኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃ መስፈርት ተመዝኖ ከመቶ ያገኘው ውጤት ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ ሊያሸጋግረው የሚችል ቢሆንም በዚህ መመሪያው ላይ የተቀመጠውን ዕድገት ደረጃ ሽግግር የሀብት መጠን ያላሟላ መሸጋገር የለበትም፡፡

## 7. <u>የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት የሚሰጥባቸው የስራ ዘርፎች</u>

የዕድገት ደረጃ የሚሰጣቸዉ በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ያወጡ እና የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት መመሪያ መሰረት በተቀመጡ የስራ ዓይነቶች ላይ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች መሆን አለበት፡፡

## 8. <u>የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት የማይሰጥባቸው የስራ ዘርፎች</u>፤

ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ አደረጃጀቱ በህብረት ስራ ማህበር የሆነ እና በየትኛውም ዘርፍ ንግድ ምዝገባና ፍቃድ ያላወጣ ከሆነ የዕድገት ደረጃ መሰጠት የለበትም፡፡

9. <u>ለጥቃቅን እና አነስተኛ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንደስትሪ የሚሰጡ የዕድገት ደረጃ ዓይነቶች</u>

1. ጥቃቅን እና አነስተኛ፡-

   ሀ) ምስረታ ወይም ጀማሪ፤

   ለ) ታዳጊ ወይም መስፋት፤

   ሐ) መብቃት፤ ሲሆኑ

2. መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንደስትሪ ናቸው፡፡

10. <u>የጥቃቅን፤ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት የመለያ ቀለማት</u>

1. ለጥቃቅን እና ለአነስተኛ ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ ነጭ ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፤
2. ለጥቃቅን ታዳጊ እና አነስተኛ ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ አረንጓዴ ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፤
3. ለጥቃቅን መብቃት እና አነስተኛ መብቃት ኢንተርፕራይዝ ቢጫ ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፤
4. ለመካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ሰማያዊ ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፤
5. ከነበረበት የዕድገት ደረጃ በመስፍረቱ መሰረት ተመዝኖ ዝቅ ያለ የዕድገት ደረጃ ላገኘ ኢንተርፕራይዝ ቀይ ሰርተፍኬት መሰጠት አለበት፤
6. ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ለሚሸጋገሩት ኢንተርፕራይዞች ደረጃውን የጠበቀ ነጭ በወርቃማ ፅሁፍ የተዘጋጀ ሰርቲፊኬት መሰጠት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ አወሳሰን እና ሽግግር መስፈርቶች</u>

11. <u>ወደ ታዳጊ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሉ የሚገቡ መስፈርቶች፤</u>

1. በሥራ ዕድል ፈጠራ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት፡-

   ሀ) በኢንዱስትሪ ስራ ዘርፍ የተሰማራ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ እስከ 3 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ

ደግሞ የደመወዝ ክፍያ ሰነድ የተከፈለ እስከ 2 ሰው መሆን አለበት፤

ለ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ጊዜያዊ የስራ ዕድል እስከ 2 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ 1 ሰው መሆን አለበት፤

ሐ) በኢንዱስትሪ ዘርፍም ሆነ በአገልግሎት የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ 6 ሰዎች መሆን አለበት፤

መ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የስራ ዕድል እስከ 5 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ እስከ 4 ሰው መሆን አለበት፤

2. በሃብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት፡-

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከብር 50,001.00 እስከ ብር 75,000.00 መሆን አለበት፤

ለ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 100,001.00 እስከ ብር 500,000.00 መሆን አለበት ፤

ሐ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50% እና በላይ መሆን አለበት፤

መ) ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50% እና በላይ ሆኖ ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙሉ ስራው ማዋል አለበት፤

ሠ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

3. በሃብት መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት፡-

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 40,000.00 መሆን አለበት፤

ለ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 50,001.00 እስከ ብር 200,000.00 መሆን አለበት፤

ሐ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ በቋሚ ንብረት የዋለው 20% እና በላይ መሆን አለበት፤

መ) ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 20% እና በላይ ሆኖ ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙለ ለስራው ማዋል አለበት፡፡

4. ትርፋማነት በኢንደስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ ቢያንስ 10 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፤

ለ) ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ20% በላይ መሆን አለበት:

5. ትርፋማነት በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ ቢያንስ 10 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፤

ለ) ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ15% በላይ መሆን አለበት፤

6. በገበያ መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ

ሀ) ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 75,000.00 እስከ ብር 100,000.00 መሆን አለበት፤

ለ) ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 150,000.00 እስከ ብር 750,000.00 መሆን አለበት፤

ሐ) ኢንተርፕራይዙ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ30% በላይ ፣ በብረታ ብረትና እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ቢያንስ ከ70% በላይ ፣ በተቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ75% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፤

መ) ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ ሦስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፤

ረ) ኢንተርፕራይዙ ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በ 1 ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት::

7. በገበያ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ) ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን እስከ ብር 75,000.00 መሆን አለበት፤

ለ) ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 75,001.00 እስከ ብር 200,000.00 መሆን አለበት፤

ሐ) ከኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ ኢንተርፕራይዙ ከ70% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግሥት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፤

መ) ኢንተርፕራይዙ ምርትና አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ ቢያንስ ሦስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፡፡

8. የኢንተርፕራይዙ ምርታማነት

ሀ) በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ምርታማነት ካለው ሙሉ የማምረት ወይንም አገልግሎት የመስጠት አቅም ቢያንስ 50% በላይ መጠቀም አለበት፤

ለ) ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 70% ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

9. በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ መሆን አለበት፤

ለ) ኢንተርፕራይዙ ለተሰማራበት የምርት እና ወይም የአገልግሎት ንግድ ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል ፣ የሂሳብ መግለጫ ማዘጋጀት ወይም ማቅረብ ኦዲት መደረግ አለበት፤

ሐ) የኢንተርፕራይዙ የማምረቻ ማዕከል አደረጃጀት የምርት ሂደትን የተከተለና ንጽህናው የተጠበቀ መሆን አለበት፤

መ) የኢንተርፕራይዙ አባላትን እና ሰራተኞችን የሥራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና እንደንውስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟላ መሆን አለበት፤

ሠ) የኢንተርፕራይዙን ሥራ ለማስፋፋት የሚያስችል በጽሑፍ የተዘጋጀ የንግድ ዕቅድ መዘጋጀት አለበት፤

ረ) ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር ስለ የንግድ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት፡፡

10.በመንግሥታዊ ድጋፎች አጠቃቀም

ሀ) የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ ያዋለ መሆን አለበት፤

ለ) የብድር ተጠቃሚ ከሆነ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር  የሌለበት መሆን አለበት፤

ሐ) የማምረቻ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት፤

መ) በመንግስት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከበ መሆን አለበት፡፡

11. በቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ለመሆን ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

ለ) ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 50% የአካባቢ ብክለት የማያስከትልና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት፡፡

12.ግዴታን ስለመወጣት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን ዓመታዊ ግብር መክፈል አለበት፤

ለ) ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፤

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ለዕድሳት እና ለዕድገት ደረጃ ሽግግር አገልግሎት ለማግኘት ሲመጣ ቀደም ሲል የተሰጠውን ነባሩን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

## 12.<u>ወደ መብቃት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶች</u>

1. በስራ ዕድል ፈጠራ

ሀ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ እስከ 5 ሰዎችን ያሰማራ ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ እስከ 5 ሰው መሆን አለበት፡፡

ለ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እስከ 3 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ እስከ 2 ሰው መሆን አለበት፡፡

ሐ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ ከ6 እስከ 15 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ6 አስከ 15 ሰው መሆን አለበት፡፡

መ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ3 እስከ 15 ሰዎች ሲሆን በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ2 እስከ 15 ሰው መሆን አለበት፡፡

2. በሃብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፡-

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሀብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከብር 75,001.00 እስከ ብር 100,000.00 መሆን አለበት::

ለ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሀብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 500,001.00 እስከ ብር 1,500,000.00 መሆን አለበት::

ሐ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50% እና በላይ መሆን አለበት፡፡

መ) ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደ ስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50% እና በላይ ሆኖ ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉ በሙሉለስራው ማዋል አለበት፣

ሠ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

3. በሃብት መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ) ጠቅላላ  የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከብር 40,001 እስከ ብር 50,000.00 መሆን አለበት::

ለ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሀብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ከብር 50,001.00 እሰከ ብር 500,000.00 መሆን አለበት::

ሐ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት የዋለው 20% እና በላይ መሆን  አለበት::

መ) ሳይበደሩ በራሳቸው ገንዘብ ወደስራ ለሚገቡ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 20% እና በላይ ሲሆን ቋሚ ንብረት ኖሯቸው ለግብዓት የሚበደሩ ሙሉበሙሉ ለስራው ማዋል አለበት፣

ሠ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

4. ትርፋማነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ 20 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ) ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ  መጠን  ከተጣራ  ሃብት ከ30% በላይ መሆን አለበት፡፡

5. ትርፋማነት በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ 20 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፣

ለ) ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን  ከተጣራ ሃብት ከ20% በላይ መሆን አለበት፤

6. በገበያ መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ

ሀ) ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 75,000.00 እስከ ብር 100,000.00 መሆን አለበት፣

ለ) አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በ1ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 500,001.00 እስከ ብር 1,500,000.00 መሆን አለበት፣

ሐ) ከኢንተርፕራይዙ በ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ35% በላይ በብረታ ብረትና እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ75% በላይ በቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ80% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፣

መ) ኢንተርፕራይዙ ሌሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ኮንትራት በ1 ዓመት ቢያንስ 2 ጊዜ የገበያ ትስስር የፈጠረ መሆን አለበት፣

ሠ) ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፣

ረ) ኢንተርፕራይዙ ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በዓመት ሶስት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት፤

7. በገበያ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ

ሀ) ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 50,001.00 እስከ ብር 75,000.00 መሆን አለበት፣

ለ) አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ 1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 200,001.00 እስከ ብር 750,000.00 መሆን አለበት፣

ሐ) ከኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ ከ85% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፣

መ) ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፤

8. ኢንተርፕራይዙ ምርታማነት

ሀ) በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ምርታማነት ካለው ሙሉ የማምረት አቅም ቢያንስ 70% በላይ መጠቀም አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ለሚያመርታቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘመናዊ የስራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ መሆን አለበት፣

ሐ) ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ወይም ወደውጪ የሚላኩ ምርቶችን ማምረት መቻል አለበት፣

መ) ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 75% ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መኖር አለበት፤

9. በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የሥራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ያደረገና ስትራቴጂክ ዕቅድ መኖር አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ለተሰማራበት የምርት እና ወይም የአገልግሎት ንግድ ሥራ የሂሳብ  መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል እና ኦዲት ማስደረግ አለበት፣

ሐ) የኢንተርፕራይዙ አባላትን እና ሰራተኞችን የሥራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟላ መሆን አለበት፣

መ) የኢንተርፕራይዙን ሥራ ለማስፋፋት የሚያስችል በጽሑፍ  የተዘጋጀ የንግድ እቅድ መዘጋጀት አለበት፣

ሠ) ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት፤

10. በመንግስታዊ ድጋፎች አጠቃቀም

ሀ) የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና የአሠራሩን ለሌሎች ተሞክሮውን ለማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ለ) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ጋር በትብብርና በኩባንያው ውስጥ ስልጠና የሚሳተፍ መሆን አለበት፣

ሐ) ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ሆኖ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት፣

መ) የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት፣

ሠ) በመንግስት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከበ መሆን አለበት፣

ረ) የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ ከሆነ የኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለበትና ከማዕከሉ ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን የፋይናንስና የማምረቻ ቦታ ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆን አለበት፤

11. በቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግልቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት::

ለ) የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት::

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 75% የአካባቢ ብክለት የማያስከትና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት፤

12. ግዴታን ስለመወጣት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን የ1 ዓመት የገቢ ግብር መክፈል አለበት::

ለ) ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዙ የተሠጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

13.<u>ወደ መካከለኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶች</u>

1. በስራ ዕድል ፈጠራ

ሀ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ ከ30 በላይ ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ20 በላይ መሆን አለበት፡፡

ለ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ20 በላይ ሰዎች ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ15 በላይ መሆን አለበት፡፡

2. በሃብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፣

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ከብር 1.5 ሚሊዮን በላይ መሆን አለበት::

ለ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ቋሚ ንብረት ያዋለው 70% እና በላይ መሆን አለበት፡፡

ሐ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

3. በሃብት መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ከብር 500,000.00 በላይ መሆን አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 40% እና በላይ መሆን አለበት፣

ሐ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

4. ትርፋማነት በኢንደስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ እስከ 30 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፡፡

ለ) ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ50% በላይ መሆን አለበት::

5. ትርፋማነት በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ሀ) በ1 ዓመት ካደረገው ሽያጭ እስከ 30 በመቶ የትርፍ መጠን ያስመዘገበ መሆን አለበት፣

ለ) ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋፋት ያዋለው ኢንቨስትመንት እና ወይም የቁጠባ መጠን ከተጣራ ሃብት ከ30% በላይ መሆን አለበት።

6. በገበያ መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ) የኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ከብር 4,500,000.00 በላይ መሆን አለበት፣

ለ) ከኢንተርፕራይዙ የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ 50% በላይ በብረታ ብረትና እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ80% በላይ እና በተቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ90% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ለሌሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ኮንትራት በ1 ዓመት ቢያንስ 5 ጊዜ የገበያ ትስስር የፈጠረ መሆን አለበት፣

መ) ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም፣

ሠ) ኢንተርፕራይዙ ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በ1 ዓመት ሁለት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት፤

7. በገበያ መጠን በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ፤

ሀ) ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ከብር 1,500,000.00 መሆን አለበት፣

ለ) ከኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ውስጥ ከ90% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፤

8. የኢንተርፕራይዙ ምርታማነት

ሀ) በኢንዱስትሪም ሆነ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ምርታማነት ካለው ሙሉ የማምረት አቅም ቢያንስ 85% በላይ መጠቀም አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ለሚያመርታቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘመናዊ የስራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ መሆን አለበት፣

ሐ) ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ማምረት መቻል አለበት፣

መ) ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 90% ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መኖር አለበት፤

9. በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ዘመናዊ የስራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ያደረገና ስትራቴጂክ ዕቅድ መኖር አለበት፡፡

ለ) ኢንተርፕራይዙ ለተሰማራበት የምርት እና ወይም የአገሎግሎት ንግድ ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል እና ኦዲት ማስደረግ አለበት፡፡

ሐ) የኢንተርፕራይዙ አባላትን እና ሰራተኞችን የስራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟላ መሆን አለበት፡፡

መ) የኢንተርፕራይዙን ሥራ ሽግግር የሚያሳይ በጽሑፍ የተዘጋጀ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል መዘጋጀት አለበት፡፡

ሠ) ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት፡፡

10. በመንግሥታዊ ድጋፎች አጠቃቀም

ሀ) የሚሰጠውን ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና የአሠራሩን ለሌሎች ተሞክሮውን ለማስተለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ለ) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ጋር በትብብርና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና የተሳተፈ መሆን አለበት፡፡

ሐ) ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ሆኖ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር የሌለበትመሆን አለበት፡፡

መ) የማምረቻ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት፡፡

ሠ) በመንግስት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከ በመሆን አለበት፡፡

ረ) ወደ ኢንዱስትሪ ዞን ለመግባት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቀ መሆን አለበት፡፡

ሰ) ከንግድና ልማት ባንኮች ለመበደር የሚያስችል የብድር ዋስትና ያዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

11. በቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎችየቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት፡፡

ለ) የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት፡፡

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 85% የአካባቢ ብክለት የማያስከትል እና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት፡፡

12. ግዴታን ስለመወጣት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል አለበት፡፡

ለ) ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፡፡

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ለዕድሳት እና ለዕድገት ደረጃ ሽግግር አገልግሎት ለማግኘት ሲመጣ ቀደም ሲል የተሰጠውን ነባሩን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

## 14. ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ የመሸጋገር ሂደት

ወደ መካከለኛ ኢንደስትሪ የሚደረገው ሽግግር ዘርፍን ፣ ካፒታልንና የተፈጠረን የስራ ዕድል መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በዚህምመሰረት፡

1. በኢንደስትሪ ዘርፍ አባላቱን ጨምሮ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል ከ30 ሰው በላይ ፣ ጊዜያዊ የስራ ዕድል ከ20 ሰው በላይ ሆኖ ካፒታል ከብር 1.5 ሚሊዮን በላይ ሲሆንና በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፤
2. በአገልግሎት ዘርፍ አባላቱን ጨምሮ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል ከ20 ሰው በላይ ፤ ጊዜያዊ የስራ ዕድል ከ15 በላይ ሆኖ ካፒታል ከብር 500,000.00 አምስት መቶ ሺ በላይ ሲሆን በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፤
3. ወደ መካከለኛ ኢንደስትሪ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ለደረጃው የሚጠበቀውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኙ የዕድገት ደረጃና ሽግግር ሂደት፡-

   ሀ) በወረዳ ደረጃ በባለሙያ የተለየውን የኢንተርፕራይዞች መረጃ በጽህፈት ቤት ፕሮሰስ ካውንስል በማጸደቅ የጸደቀበትን ቃለ ጉባኤ በጽህፈት ቤት ሃላፊው ተረጋግጦ ለክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት መላክ አለበት፡፡

   ለ) የክፍለ ከተማው ደረጃ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ባለሙያ ከወረዳ የደረሰውን መረጃ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለፕሮሰስ ካውንስል አቅርቦ በማጸደቅ የጸደቀበትን ቃለ ጉባኤ በጽህፈት ቤት ሃላፊው ተረጋግጦ ለስራ፤ ለቢሮው መላክ አለበት፡፡

   ሐ) ከየክፍለ ከተሞች የደረሰውን መረጃ ትክክለኛነቱን በስራ ሂደቱ በማረጋገጥ ለፕሮሰስ ካውስል አቅርቦ በማጸደቅ ኢንተርፕራይዞች እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

   መ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለዉ የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

## 15. ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶች

1. በስራ ዕድል ፈጠራ

   ሀ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው ቋሚ የሥራ ዕድል

የኢንተርፕራይዝ አባላቱን ጨምሮ 101 በላይ ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ31 በላይ መሆን አለበት፡፡

ለ) በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ በጊዜያዊነት የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ 31 ሰዎች በላይ ሆኖ በአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ21 በላይ መሆን አለበት፡፡

2. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ወይም አምራች ኢንዱስትሪ የሃብት መጠን፡-

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ከብር 20,000,000.00 ብር በላይ መሆን አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 70 በመቶ እና በላይ መሆን አለበት፣

ሐ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም የኦዲት ሪፖርት ህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

3. በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የሀብት መጠን፡-

ሀ) ጠቅላላ የሃብት መጠን የተጣራ ሃብት እና ዕዳን የሚያካትት ሆኖ ከብር 5,000,000.00 በላይ መሆን አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ በብድር ካገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት ያዋለው 50 በመቶ እና በላይ ሲሆንና በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ሐ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም የኦዲት ሪፖርት ህጋዊ እውቅና ባለው የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

4. ትርፋማነት የሀብት መጠን

በአገልግሎት ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ትርፋማ መሆኑ መታየት አለበት፡፡

5. በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ የገበያ መጠን፡-

ሀ) ከኢንተርፕራይዙ ወይም ከኢንዱስትሪው የ1 ዓመት የሽያጭ መጠን ውስጥ በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ 55 በመቶ

በላይ በብረታ ብረትና እንጨት ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቢያንስ ከ80 በመቶ በላይ እና በተቀሩት ዕድገት ተኮር ንዑሳን ዘርፎች የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከ90 በመቶ በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ለሌሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ኮንትራት በ1 ዓመት ቢያንስ 5 ጊዜ የገበያ ትስስር የፈጠረ መሆን አለበት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፣

መ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ለደረጃው በተዘጋጀ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ቢያንስ በ1 ዓመት ሁለት ጊዜ የተሳተፈ መሆን አለበት::

6. በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ የሀብት መጠን፡-

ሀ) ከኢንተርፕራይዙ ወይም ከኢንዱስትሪው ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ውስጥ ከ90% በላይ የተገኘው ሽያጭ ከመንግስት የገበያ ትስስር ውጪ መሆን አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ምርት ለማስተዋወቅ ቢያንስ አምስት ዓይነት ውጤታማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፤

7. የኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ምርታማነት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ለሚያመርታቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ዘመናዊ የስራ አመራርን የተከተለ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የዘረጋ መሆን አለበት፣

ለ) ለገቢ ወይም ለወጪ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን ወይም ገቢ ምርቶችን የሚተካ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ማምረት መቻል አለበት፣

ሐ) ከኢንተርፕራይዙ አባላት እና ወይም ቋሚ ሰራተኞች ቢያንስ 90 በመቶ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መኖር አለበት፤

8. በተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ዘመናዊ የስራ አመራር ዘይቤ ተግባራዊ ያደረገና ስትራቴጂክ ዕቅድ መኖር አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው ለተሰማራበት የምርት፣ የአገልግሎት ወይም ንግድ ሥራ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥራ ላይ ማዋል እና ኦዲት ማስደረግ አለበት፣

ሐ) የኢንተርፕራይዙ ወይም ኢንዱስትሪው አባላትን እና ሰራተኞችን የስራ ደህንነት ለመጠበቅ የሥራ ልብስ እና እንደ ንዑስ ዘርፉ ዓይነት የደህንነት መሣሪያዎች የተሟሉ መሆን አለበት፣

መ) የኢንተርፕራይዙን ወይም ኢንዱስትሪውን ሥራ ሽግግር የሚያሳይ በጽሑፍ የተዘጋጀ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል መዘጋጀት አለበት፣

ሠ) ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ጋር ስለ ቢዝነስ ሥራ ሃሳብ ለመለዋወጥም ይሁን የጋራ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ግንኙነት መፍጠር አለበት፤

9. በመንግሥታዊ ድጋፎች አጠቃቀም

ሀ) ከፌደራልና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እና ከተለያዩ ኢንስቲቱቶችና ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠውን ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተግባር ላይ አውሎ ተጨባጭ ለውጥ ያመጣና አሠራሩንና ሌሎች ተሞክሮውን ለማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ለ) ከኢንስቲቱቶች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ጋር በትብብርና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና የተሳተፈ መሆን አለበት፡፡

ሐ) ብድር ተጠቃሚ ከሆነ ተደጋጋሚ የብድር ተጠቃሚ ሆኖ ያልተመለሰ ውዝፍ ብድር የሌለበት መሆን አለበት::

መ) የማምረቻ ማዕከል ተጠቃሚ ከሆነ የውል ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ መሆን አለበት::

ሠ) በመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት የሚሰጠውን የገበያ ትስስር በገባው ውል  በአግባቡ እየሰራ ያለ ወይም ሰርቶ ያስረከበ መሆን አለበት፡፡

ረ) ወደ ኢንዱስትሪ ክላስተር ወይም ፓርክ ለመግባት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቀና ፈቃደኛ መሆን አለበት፡፡

ሰ) ከንግድና ከልማት ባንኮች ለመበደር የሚያስችል የብድር ዋስትና ያዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

10. በቴክኖሎጂ አጠቃቀም

ሀ) ኢንተርፕራይዙ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማሻሻል በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶችና ሌሎች የቴክኖሎጂ ተቋማት የሚሰራጩ ተፈላጊና አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ መሆን አለበት፣

ለ) የምርትና አገልግሎት ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ወቅታዊና የተሻሻለ አሠራር ተጠቃሚ መሆን አለበት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዙ ከሚጠቀምባቸው የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ውስጥ ቢያንስ 90 በመቶ የአካባቢ ብክለት የማያስከትሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መሆን አለበት፤

11. የሥራ ቦታ ምልከታ እና ከስራ ላይ ደህንነት አኳያ

ሀ) የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ መሆን አለበት፣

ለ) የደህንነት አልባሳትና ቁሳቁስ መጠቀም አለበት፣

ሐ) የአደጋ ጊዜ መውጫ በሮች ማዘጋጀት አለበት፣

መ) የተደራጀ የቁሳቁሶች አቀማመጥ መኖር አለበት፣

ሠ) በቂ አየር እና ብርሃን ያለው የማከማቻ ቦታ ያዘጋጀ መሆን አለበት፤

12. ግዴታን ስለመወጣት

ሀ) ኢንተርፕራይዙ የሚጠበቅበትን ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል አለበት፣

ለ) ኢንተርፕራይዙ ዓመታዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማካሄድ አለበት፣

ሐ) ኢንተርፕራይዙ የተሠጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት መመለስ አለበት፡፡

## 16. ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የመሸጋገር ሂደት

ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ሽግግር ዘርፍን፣ ካፒታልንና የተፈጠረን የስራ ዕድል መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡-

1. በኢንዱስትሪ ዘርፍ አባላቱን ጨምሮ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል ከ101 ሰው በላይ፣ ጊዜያዊ የስራ ዕድል ከ31 ሰው በላይ ሆኖ ካፒታሉ በኢንዱስትሪ ከብር 20,000,000.00 በላይ ሲሆንና በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፤
2. በአገልግሎት ዘርፍ አባላቱን ጨምሮ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ቋሚ የስራ ዕድል ከ31 ሰው በላይ፤ ጊዜያዊ የስራ ዕድል ከ21 በላይ ሆኖ ካፒታሉ ከብር ከ5,000,000.00 በላይ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፤
3. ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ለደረጃው የሚጠበቀውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኙ የዕድገት ደረጃና ሽግግር ሂደት፡-

   ሀ) ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚደረግ ሽግግር የሚከናወነው በከተማ ደረጃ ብቻ ነው፣

   ለ) የከተማው የኢንተርፕራይዞች ሽግግርና ተሞክሮ ቅመራ ዳይሬክቶሬት ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን በከተማው ባለሙያዎች በመስፈርቱ መሰረት ይለያል፣

   ሐ) የከተማው የኢንተርፕራይዞች ሽግግርና ተሞክሮ ቅመራ ዳይሬክቶሬት በባለሙያ የተለየውን የኢንተርፕራይዞች መረጃ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለዘርፍ ኃላፊ አቅርቦ በዘርፍ በማጸደቅ የጸደቀበትን ቃለ ጉባኤ በዘርፍ ሃላፊው ተረጋግጦ ለዋና ቢሮው ኃላፊው መቅረብ አለበት፣

   መ) ከዘርፍ የደረሰውን መረጃ ቢሮው ለፕሮሰስ ካውስል አቅርቦ በማጸደቅ ኢንተርፕራይዞች እውቅና እንዲያገኙ ማደረግ አለበት፣

   ሠ) የሃብትና የዕዳ መግለጫ ወይም ኦዲት ሪፖርት በህጋዊ እውቅና ባለዉ የሂሳብ አዋቂ ባለሙያ ወይም በኦዲት የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ለኢንተርፕራይዞችና የዕድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ ድጋፍ አሰጣጥ

### 17. በምሥረታ ወይም ጀማሪ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ

1. የመነሻ ካፒታል ማመቻቸት

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመመሥረት ፍላጐት ያላቸው በቅድሚያ የራሳቸው ቁጠባ እንዲኖራቸው ማበረታታት፣ የራሳቸው ቁጠባ ያላቸው ብድር ቅድሚያ የሚያገኙበት አሠራር ይመቻቻል፣

ለ) ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትና ከዩኒቨርሲቲ የሚወጡ ወጣቶች ቤተሰቦቻቸው የቁጠባ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው የማበረታታት ሥራ ይሰራል፣

ሐ) በአዲስ መልክ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የሚያቋቁሙ ወጣቶች ልማታዊ በሆነ መልኩ ለመነሻ የሚሆን ካፒታል እንዲያከማቹ ከመንግስት ኘሮጀክቶችና ኘሮግራሞች ተጠቃሚ እንዲሆኑና እንዲቆጥቡ የሚያስችል አሠራር ተግባራዊ ይደረጋል፣

መ) የወሰዱትን ብድር በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ በመደገፍና የመልካም ተበዳሪነት ታሪክ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

ሠ) ለተበዳሪነት የሚያበቃቸው የስራ ዕቅድ ዝግጅት ድጋፍ ይደረጋል፤

2. ሕጋዊ አቋም እንዲኖራቸው ማብቃት

ሀ) በምስረታ ደረጃ ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመረጡት ህጋዊ አደረጃጀት ተጠቅመው እንዲቋቋሙ ድጋፍ ይደረጋል፣

ለ) በሁሉም ዓይነት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ህጋዊ ግብር ከፋይ መለያ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማውጣት በሚያስፈልግባቸው የስራ ዘርፎች እንዲያወጡ ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ይደረጋል፣

መ) በምስረታ ደረጃ ያሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ህጋዊ የንግድ ሥርዓትና አሠራርን ተከትለው እንዲሠሩ መደገፍና ሕጋዊ የንግድ ፈቃድና ምዝገባ እንዲኖራቸው ይደረጋል፤

3. የቢዝነስ ሥራ አመራር ሂሳብ አያያዝና የገበያ ብቃት ማሳደግ

   ሀ) ኢንተርፕራይዞቹ መሠረታዊ የቢዝነስ ሥራ አመራርና ኢንተርፕሪነርሺፕ ክህሎት እንዲኖራቸው ይመቻቻል፣

   ለ) መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ስልጠናዎችን መስጠትና ሞዴል የሂሣብ አያያዝ ማኑዋሎችን በማዘጋጀት እንዲጠቀሙ ይመቻቻል፣

   ሐ) የአካባቢ ገበያ በፍትሃዊ መንገድ እንዲተሳሰሩ የመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክት መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የግል ባለሀብት የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በጥናት በመለየት የስራ ትስስር እንዲያገኙ ድጋፍ ይመቻቻል፣

   መ) ጥሬ ዕቃ አቅርቦት ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር ድጋፍ እንዲያገኙ ይመቻቻል፣

   ሠ) ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ካይዘን ድጋፍ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣

   ረ) በማምረት ዘርፎች ላይ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የመሳሪያ ሊዝ ድጋፍ እንዲያገኙ ይመቻቻል ፣

   ሰ) የኢንተርፕራይዞቹን የሥራ ባህሪይ መሠረት ያደረገ የመስሪያና መሸጫ ቦታ ይመቻቻል፣

   በ) ልምድ ካላቸው ነባር ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

   ተ) በዘርፍ የባለሙያ ሙያዊ ድጋፍ ምክር እንዲያገኝ መደረግ አለበት፤

4. በምስረታ ደረጃ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራ ለመጀመር የሚያስችላቸውና ምርታማነታቸውንና የምርት ጥራታቸውን የሚያሳድጉ የክህሎትና የቴክኒክ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

18. <u>በታዳጊ ወይም መስፋፋት ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ</u>

1. የፋይናንስ ድጋፍ ማመቻቸት

   ሀ) በታዳጊ ደረጃ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ተከታታይና ከሥራ ባህሪያቸው ጋር የሚጣጣም የብድር አቅርቦት ይመቻቻል፤

   ለ) ኢንተርፕራይዞቹ  የወሰዱትን ብድር በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ መደገፍና የመልካም ተበዳሪነት ታሪክ እንዲኖራቸው ይደረጋል፤

ሐ) ኢንተርፕራይዞቹ ለተበዳሪነት የሚያበቃቸው የስራ ዕቅድ ዝግጅት ድጋፍ ይደረጋል፡፡

2. የተጠናከረ የክህሎት ቴክኖሎጂ ድጋፍ ማድረግ፣

ሀ) የገበያ ፍላጐትን ታሳቢ ያደረገ የክህሎት ማበልጸጊያና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ማመቻቸት፣

ለ) በገበያ ላይ በቀጣይነት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሙያ ብቃት እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ድጋፍ ይሰጣል፣

ሐ) በጥናት ላይ የተመሠረት የስራ አመራር ስልጠና በመስጠት የኢንተርፕራይዞቹን የቢዝነስና ሥራ አመራር ብቃት በአስተማማኝ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ይደረጋል፣

መ) የምርትና አገልግሎት ጥራትና ምርታማነት ሥራ አመራር ወይም ካይዘን በኢንተርፕራይዞች እንዲተገበር ማስቻል፣

ሠ) የክልል ገበያን እንዲሁም የአካባቢ ገበያ ትስስር መፍጠርና የገበያ አቅም ማሳደጊያ መድጋፍ መስጠት፣

ረ) የገበያ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ማድረግ፣

ሰ) ተወዳዳሪነትን ማሳደግ የሚያስችል የማሽነሪ ሊዝ ድጋፍ ማድረግ፣

በ) የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ከከፍተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰር ስራ መሰራት፣

ተ) ከመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ተሞክሮ እንዲወስድ ማድረግ፤

3. የመስሪያና መሸጫ ማዕከላትን ማስፋፋት

ሀ) የኢንተርፕራይዞቹን የሥራ ባህሪይ መሠረት ያደረገ የመሥሪያና መሸጫ ማዕከላት ተመጣጣኝ አገልግሎት ኪራይ እንዲከፍሉ ማድረግ፣

ለ) ኢንተርፕራይዞቹ ለሚጠቀሙበት የመሥሪያና መሸጫ ማዕከላት ተመጣጣኝ የአገልግሎት ኪራይ እንዲከፍሉ ማድረግ፣

ሐ) በመሥሪያና መሸጫ ማዕከላት ውስጥ ኢንተርፕራይዞቹ በራሳቸው ሊያሟሉ የማይችሏቸውን በጋራ መጠቀም እንዲችሉ የጋራ መገልገያ አገልግሎቶችን ማጠናከር ፤

4. ህጋዊ ማድረግ

ሀ) ኢንተርኘራይዞቹ በህጋዊ የንግድ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ እንዲሠሩ መደገፍ፡፡

ለ) ኢንተርኘራይዞቹ በወቅቱ ግብር እንዲከፍሉ ማድረግ ፣

ሐ) በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆን ሀገራዊና አለም አቀፍ አስገዳጅ ደረጃዎችን እንዲያሟሉ መደገፍ፡፡

## 19. <u>በመብቃት ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ</u>

1. ተወዳዳሪ የሆነ ኢንተርኘራይዝ መፍጠር

ሀ) ቀጣይነት ያለው የጥራትና ምርታማነት ብቃት ማሳደጊያ ወይም ካይዘን ሥርዓትን መትከል፣

ለ) ገበያን የማስፋፋት ድጋፍ ማድረግ፣

ሐ) በገበያ ውስጥ ኢንተርኘራይዞቹ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አዳዲስ የምርት ልማት ሥራዎችን እንዲያካሂዱ ማመቻቸት፣

መ) ኢንተርኘራይዞቹ ለተሠማሩበት ዘርፍ የሚያስፈልገውን ዘመናዊ ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማመቻቸት ፣

ሠ) በዋናነት የውጭ ገበያ ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ድጋፍ ማድረግ፣

ረ) ስራቸውን ለማስፋፋት የብድር አገልግሎት ማመቻቸት፣

ሰ) ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድግ የቴክኖሎጂ ድጋፍ ማመቻቸት፣

በ) ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ተሞክሮ ልውውጥ እንዲያገኝ ማመቻቸት፤

2. ኢንተርኘራይዞቹ ወደ መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች ሊያሸጋግራቸው የሚያስችላቸውን የማምረቻ መሣሪያ ዓይነቶች መለየትና በመሳሪያ ሊዝ ሥርዓት እንዲጠቀሙ ማመቻቸት፤

3. ያለውን የስራ ባህሪይና የማምረቻ ማዕከላትን መሰረት ያደረገ የማምረቻ ማስፋፊያ ቦታ ድጋፍ ማድረግ ብዛት ማዕከላትን ማስፋፋት፡፡

## 20. <u>መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች የሚሰጡ ድጋፎች ፤</u>

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ስትራቴጂ የተመለከቱትን የድጋፍ ማዕቀፎች ለመተግበር በወጡት የማስፈፀሚያ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች መሠረት

መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በደረሱበት ዕድገት ደረጃ ይገጥሟቸዋል ተብሎ ለሚታሰቡ ዋና ዋና ችግሮች የሚከተሉት ድጋፎች ተቀርጸዋል፡፡

1. የማምረቻና መሸጫ ቦታን በተመለከተ፡-

ሀ) ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን ብዛትና ዓይነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀጣይ ዓመታት ለእነዚህ ኢንተርፕራይዞች በጠቅላላው ለኢንዱስትሪ መንደሮች ከሚከለለው ቦታ ከ10 እስከ 20 ፐርሰንት የሚሆነውን በዕቅድ እንዲያዝ  ይደረጋል፣

ለ) ከአነስተኛ ወደ መካካለኛ ለሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ በሚዘጋጀው ቦታ ለመሠረተ ልማት ግንባታ የሚሆን በጀት በመመደብ የተሟላ መሠረተ  ልማት እንዲኖር ይደረጋል፣

ሐ) ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ከማምረቻ ማዕከላት የመውጫ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ በኢንዱስትሪ መንደሮች ለእያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ እንደ ሥራው ባህሪ አስቀድሞ ቦታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፣

መ) እንደ ኢንተርፕራይዞች የሥራ ባህሪ የማምረቻ ህንጻ ወይም ሼድ በተመጣጣኝ የኪራይ ዋጋ ማቅረብ ወይም ራሳቸው እንዲገነቡ ቦታ ማመቻቸት፣ ይህ ድጋፍ እስኪመቻችላቸው ድረስ በጊዜ ተገድቦ በነበሩበት ሼድ የመምረት ስራቸውን እንዲቀጥሉ ይደረጋል ፣

ሠ) እንደ ኢንተርፕራይዞቹ የስራ ባህሪና አቅም የሚሰጣቸው ቦታ ከ500 ካሜ እስከ 2000 ካሜ እንዲሆን ይደረጋል፣

ረ) የከተማ አስተዳደሩ በመካከለኛ ወጪ በሚያስገነባቸው ክላስተር ማእከላት በተመጣጣኝ ኪራይ እና በጊዜ ለተወሰነ ገብተው የሚያመርቱበትን ሁኔታ እንድመቻች ይደረጋል፤

2. የፋይናንስ  አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ፣

ሀ) ኢንተርፕራይዞች ለሥራ እንቅስቃሴያቸው ማስፋፊያ የሚፈለገውን ብድር የካፒታልና መሣሪያ አቅማቸውን ለማጐልበት ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ በተዘጋጀው  ልዩ የብድር ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

ለ) ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በማጠናቀር የፋይናንስ ፍላጐታቸውን ይለያል፣

ሐ) አበዳሪ ባንኮች የሚጠይቁት የብድር ቅድመ ሁኔታ ለኢንተርፕራይዞች ምቹ እንዲሆን ከአካባቢ ባንኮች ጋር መወያየትና በቅንጅት ይሰራል፣

መ) ኢንተርፕራይዞችን የባንክ ብድር ለማግኘት እንዲችሉ የቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀት ረገድ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ይሰጣል፣

3. የገበያ ልማት ድጋፍና የመንግስት ግዢ ስርዓትና የንዑስ ተቋራጭነት አሰራር እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር ማሻሻል በተመለከተ፣

ሀ) ኢንተርፕራይዞቹ በተሰማሩበት መስክ ከአቅም ጋር የሚመጣጠን ሥራዎችን በመለየት በስፋት ከመንግስት ፕሮጀክቶች የገበያ እድል ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን አሰራር ይዘረጋል፣

ለ) ከነባር መካከለኛና ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ በቂ አቅም ያላቸውን በመለየት የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈራረሙ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

ሐ) ወቅታዊ የገበያ መረጃ የሚያገኙበትን አሰራር ይዘረጋል፡፡

4. የሰው ኃይል ልማትና የቴክኖሎጂ ዕድገት ድጋፍ በተመለከተ፣

ሀ) በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፉ ባሉ የፌደራል ኢንስቲትዩት የክህሎት ማሻሻያ ሥልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፣

ለ) ኢንተርፕራይዞቹ በራሳቸው አቅም ሊገዙአቸው ያልቻሉትን የማምረቻ መሳሪያዎች ከካፒታል እቃዎች ሊዝ ኩባኒያ /ከልማት ባንክ/ በኪራይ ወይም በግዥ ሊገለገሉ እንዲችሉ ማመቻቸት፣

ሐ) በአዲስ አበባ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች እንዲሁም ከምረታማነት ማሻሻያ ተቋም ጋር ኢነተርፕራይዞቹ ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናና የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲያገኙ ማመቻቸት፣

መ) ኢንተርፕራይዞች ለሥራቸው የሚያገለግሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች በፌደራል

ደረጃ በተቋቋሙ ኢንስቲትዩቶችና በቴክኖሎጂ ፋኩሊቲዎች እንዲመነጩ ክትትል በማድረግ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ማድረግ፣

ሠ) የኢንተርፕራይዞችን የሂሣብ መዝገብ አያያዝና የቴክኖሎጅ ሽግገር የተሟላ እንዲሆን ተከታታይነት ያለው ሥልጠናና ድጋፍ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲያገኙ ማመቻቸት፤

5. የግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ፣

የግብዓት አቅርቦት ችግር መኖር ኢንተርፕራይዞች በገበያ ላይ ተወዳዳሪ መሆን እንዳይችሉ ከሚደርጉት ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ችግሩን ለማቃለል፡-

ሀ) በከተማው በየደረጃው የሚገኙ ኢንተርፕራይቾች በየስራ መስካቸው ህብረት እንዲፈጥሩና በየዘርፉ በማህበር እንዲደራጁ ማድረግ ፤

ለ) በየደረጃው የተመሰረቱ መካከለኛ ህብረት በአካባቢያቸው ከሚገኙ የዘርፍ ማህበራት ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ መድረክ ማመቻቸት፤

ሐ) በየጊዜው ኢንተርፕራይዞቹ የሚፈልጓቸውን የጥሬ ዕቃ ዓይነቶች ዝርዝር መረጃ መሰብሰበ፤

መ) በተሰበሰበው መረጃ መሠረት እንደ ፍላጎታቸው ጥቅል የጥሬ ዕቃ ግዢ ለመፈጸም የሚያስችል የኢንተርፕራይዞችና ግብዓት አቅራቢዎች የመግባቢያ ሰነድ ማዘጋጀት፡፡

6. የመሰረተ ልማት አቅርቦትን በተመለከተ

ሀ) በቀላሉ ግብዓት ለማቅረብና ምርትን ወደገበያ ለማውጣት እነዲሁም የግንባታ ዕቃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል የመንገድ አውታር ለኢንዱስትሪ በተከለሉት አካባቢዎች አስቀድሞ ሟሟላት፣

ለ) በኢንዱስትሪ መንደሮቹ ለግንባታና ለማምረቻ የሚሆን የሀይል አቅርቦት ማመቻቸት፣

ሐ) በኢንዱስትሪ መንደሮቹ ለግንባታ፤ ለማምረቻና ለመጠጥ የሚሆን የውሀ አቅርቦት እንዲኖር ማመቻቸት፣

መ) ለገበያና ለመረጃ ተደራሽነት ምቹ የሆነ የኢንተርኔትና የስልክ መሰረተ ልማት እንዲዘረጋ ማመቻቸት፡፡

# ክፍል አምስት

# የፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 21. የቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

ለቢሮው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 74/2014 የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ስትራቴጅውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ያዘጋጃሉ ፣ ያሻሽላል፣ አፈጻጸምን ይከታተላል፣
2. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ስትራቴጅውን መስረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ላይ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን ይሰራል ፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ፤
3. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የወጡ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈፃፀም የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፣
4. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የድጋፍ ማዕቀፎችን በዕድገት ደረጃቸውና በተቀመጠው የድጋፍ አይነት እና መጠን መስረት ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ይከታተላል፣የጠራ መረጃ ይይዛል ፣ እንዲያዝ ያደርጋል፣
5. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ መስፈርቱን አሟልተው ሲገኙ ወደ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ የዕውቅና ሰርተፊኬት በመስጠት ያሸጋግራል፣ ለሚመለከታቸው ተቋማት መረጃውን ይሰጣል፣
6. ለጥቃቅን ፣አነስተኛ ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ከጀማሪ እስከ መብቃት የተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት በመመሪያ መሰረት መሆኑን ይከታተላል፣
7. በጥቃቅን፣ አነስተኛ፣መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ እና የሽግግር ሂደት መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታ በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት መሰረት እንዲስተናገድ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣

8. የዕድገት ደረጃን በተመለከተ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ይፈታል ፣ እንዲፈታ ያደርጋል፤

9. የዕድገት ደረጃ የተሰጣቸውን ኢንተርፕራይዞች መረጃ አጠናክሮ ይይዛል፤ መረጃውን ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፤

10. የኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መለያ ቁጥር ያለው ማህደር በወረዳዎች እንዲከፈቱና የግብር ከፋይነት ሰርቲፊኬት፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰርቲፊኬት፤ የፀደቀ የመመስረቻ ፅሁፍ፤ የፀደቀ የመተዳደሪያ ደንብ፤ የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት፤ ከኢንተርፕራይዙና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪ ጋር የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጥ ቀሪዎችን፣ ኮፒዎች፣ ተመሳሽ የዕድገት ሰርቲፊኬት … ወዘተ በማያያዝ በአግባቡ እንዲጠበቁ ክትትል፤ ድጋፍ እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

11. የኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መረጃዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጋ እና እንዲተገበር ክትትል ፤ ድጋፍ እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

12. በመደበኛ ድጋፍ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማድረግ ያልቻለ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲረግላቸው መረጃውን በማደራጀት ለባለድርሻ አካላት ይሰጣል፤

13. ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅን፤ አነስተኛ፤ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚሰጡትን ድጋፍ የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 22.<u>የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የዕድገት ደረጃ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ግብዓት ይሰጣል ፤ የወጡትን ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤
2. ለባለሙያዎች፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ባለድርሻ አካላት ስትራቴጂውን መስረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ላይ ግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
3. ለኢንተርፕራይዞች እየተሰጠ ያለው የድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤

4. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ መስፈርቱን አሟልተው ሲገኙ ወደ መካከለኛ የዕድገት ደረጃ የሚሸጋገሩትን መረጃ አጠናክሮ በፕሮሰስ ካውንስል በማስወሰን ለቢሮ ይልካል፤

5. ለጀማሪ፣ ለታዳጊ እና መብቃት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት በመመሪያ መሰረት መሰራቱን ይከታተላል ፤ድጋፍ ያደርጋል፤

6. በዕድገት ደረጃ እና ሽግግር አሰራር ላይ የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታዎች በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መሰረት እንዲስተናገድ ያደርጋል ፡ ይከታተላል፤

7. የዕድገት ደረጃን በሚመለከት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ችግሮቹ እንዲፈቱ ያደርጋል ፣ ይከታተላል ፡፡ ችግሩ የመመሪያ ከሆነ ለከተማው የጥናቱን ውጤት ከነመፍትሄው ያመለክታል፤

8. የዕድገት ደረጃ የተሰጣቸውን ኢንተርፕራይዞች መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል ፤ መረጃውን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል ፤

9. በመደበኛ ድጋፍ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማድረግ ያልቻሉ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግላቸው መረጃውን በማደራጀት ለሚመለከተው ፈጻሚና ባለድርሻ አካል ይሰጣል፤

10. የኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መለያ ቁጥር ያለው ማህደር በወረዳዎች እንዲከፈቱና የግብር ከፋይነት ሰርቲፊኬት፣ የንግድ ምዝገበና ፈቃድ ሰርቲፊኬት፣ የፀደቀ የመመስረቻ ፅሁፍ፣ የፀደቀ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት፣ ከኢንተርፕራይዙና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪ ጋር የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጥ ቀሪዎችን፣ ኮፒዎች፣ ተመላሽ የዕድገት ሰርቲፊኬት፣..ወዘተ በማያያዝ በአግባቡ እንዲጠበቁ ክትትል፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

11. የኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መረጃዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጋ እና እንዲተገበር ክትትል፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

12. የሚመለከታቸው ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን ድጋፍ የኢንተርፕራይዞቹን የዕድገት ደረጃ

መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

23. <u>የወረዳ ጽህፈት ቤት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪ ስትራቴጂውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ግብዓት ይሰጣል፤ የወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንደስትሪ ስትራቴጂውን መሰረት በማድረግ የዕድገት ደረጃ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ላይ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፣
3. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንደስትሪ የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈፃፀም የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን ክትትል በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፤
4. ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር መስፈርቱን ያሟሉኢንተርፕራይዞችን መረጃ አጠናቅሮና አደራጅቶ በፕሮሰስ ካውንስል በማስወሰን ለክፍለ ከተማ ይልካል ፤
5. ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጀማሪ ፣ ታዳጊ እና መብቃት እና የከፍተኛ ኢንዱስትሪ የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት በመመሪያ መሰረት ይሰጣል፤
6. ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንደስትሪ የዕድገት ደረጃ እና የሽግግር ሂደት መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታ እና አቤቱታ በቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት መሰረት እንዲስተናገዱ ያደርጋል፤
7. ለጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንደስትሪ የዕድገት ደረጃ በሚመለከት የሚያጋጥሙ ችግሮች በጥናት እንዲፈቱ ለግብዓት የሚሆን መረጃ ይሰበስባል፤
8. በመደበኛ ድጋፍ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማድረግ ያልቻለ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግላቸው መረጃውን በማደራጀት ለፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ይሰጣል፤
9. ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን ድጋፍ የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይከታተላል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤

10. የኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መለያ ቁጥር ያለው ማህደር በመክፈት የግብር ከፋፋይነት ሰርቲፊኬት፤ የንግድ ምዝገበና ፈቃድ ሰርቲፊኬት፣ የፀደቀ የመመስረቻ ፅሁፍ፣ የፀደቀ የመተዳደሪያ ደንብ ፣ የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት፣ ከኢንተርፕራይዙና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪ ጋር የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጥ ቀሪዎችን፣ ኮፒዎች፣ ተመላሽ የዕድገት ሰርቲፊኬት እና ሌሎችንም በማያያዝ በአግባቡ እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
11. የኢንተርፕራይዞች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መረጃዎች በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጋ እና እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## መብትና ግዴታዎች

### 24.የጥቃቅን ፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንደስትሪ መብት፤

1. በዕድገት ደረጃ አሰጣጥና ሽግግር አሰራር ሥርዓት መሰረት ለደረሱበት የዕድገት ደረጃ መስፈርቱን አሟልቶ ሲገኝ የዕድገት ደረጃ ሰርቲፊኬት ማግኘት ይችላል፤
2. በተሰጣቸው የዕድገት ደረጃ እውቅና ሰርተፊኬት መሰረት በደረሰበት ደረጃ የሚሰጠውን ድጋፍ ማግኘት ይችላል፤
3. በዕድገት ደረጃ አሰጣጥ እና ሽግግር እንዲሁም የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረገ ድጋፍ አሰጣጥ ላይ ቅሬታና አቤቱታ በአሰራር ሥርዓት መሰረት ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት ይችላል፡፡

### 25.የጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ኢንደስትሪ ግዴታ

1. ኢንተርፕራይዙ ለዕድገት ደረጃ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች እና መረጃዎች በማሟላት በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ሳይደብቅ በግልጽ መስጠት አለበት፤
2. ኢንተርፕራይዙ የተሰጠውን የዕድገት ደረጃ በዓመቱ ወቅቱን ጠብቆ ማሳደስ አለበት፤
3. የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎችን በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል አለበት፤
4. የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሲያደርግ በፊት የተሰጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት መመለስ አለበት፤
5. የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት የጠፋባቸው ለአካባቢው ፖሊስ አመልክቶ የጠፋበት መሆኑን አስመስክሮ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## 26.የዘርፉ አመራር እና ፈጻሚ መብት፤

1. የዕድገት ደረጃ ለመስጠት የሚያስችል መረጃዎችን ከኢንተርፕራይዙና ከሌሎች አጋዥ ሴክተሮች መጠየቅና መውሰድ ይችላል ፤
2. የተሰጡ ድጋፎች የዕድገት ደረጃን መሰረት ያደረጉ ስለመሆኑ የመጠየቅና ማረጋገጥ ይችላል፡፡

## 27.የዘርፉ አመራር እና ፈጻሚ ግዴታ፤

1. በዕድገት ደረጃ መስፈርት እና በአሰራሩ ዙሪያ ለኢንተርፕራይዞች መረጃ እና ግንዛቤ መስጠት አለበት፤
2. የሚሰጡ የዕድገት ደረጃ እና ድጋፎች የአሰራር ሥርዓቱን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ አለበት፤
3. ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቶችና ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ መሰረት የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ተሰጥቷቸው በየዓመቱ ሰርቲፊኬት የማደስ እና የበፊቱን የተሰጣቸውን ሰርቲፊኬት እንዲመልሱ መደረግ አለበት፤
4. ለኢንተርፕራይዞች የተሰጣቸውን የዕድገት ደረጃ መረጃ በዓይነት፣ በስራ ዘርፍ፣ በዕድገት ደረጃ አደራጅቶ የመያዝ፤ የመተንተን እና የማሰራጨት ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል ሰባት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 28.የተጠያቂነት ሥርዓት

1. ፈጻሚ አካል

   የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ መስፈርት ሳይከተል የዕድገት ደረጃ የሰጠ ወይም ያደሰ ወይም ድጋፍ የሰጠ አመራር ወይም ፈፃሚ በህግ ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡

2. ኢንተርፕራይዝ

   የኢንተርፕራይዙን የዕድገት ደረጃ ለመስራት መረጃ ሲሰበሰብ የተሻለ የዕድገት ደረጃ ለማግኘት ወይም የዕድገት ደረጃውን ዝቅ ለማድረግ ወይም ከፍ ያለ ደረጃ ሊመወሰድ ሲባል የተሳሳተ መረጃ የሠጠ ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረበ ኢንተርፕራይዝ እንደየጥፋቱ ደረጃ አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ በህግ ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡

## 29.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች</u>

1. የዕድገት ደረጃ አወሳሰን እና ሽግግር መመሪያ ቁጥር 73/2014 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፤
2. ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ቢሮው ያወጣቸው ማንኛውም መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 30.<u>መመሪያ ስለማሻሻል</u>

ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 31. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም**

**ጃንጥራር ዓባይ ይግዛው**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባ እና**
**የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ**

## የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር መስፈርቶችና መመዘኛ ነጥቦች አባሪዎች

### አባሪ 1:-

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ከኢንተርፕራይዞች ሽግግር ደረጃዎች አንፃር ለመስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ በመቶኛ/%/ | | | መስፈርቶቹ የሚለኩባቸው ስልቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወደ ታዳጊ | ወደ መብቃት | ወደ ታዳጊ መካከለኛ | |
| **1** | **ሥራ ዕድል ፈጠራ** | **20** | **25** | **25** | ፔይ ሮልን መነሻ በማድረግ በቁጥር |
| 1.1 | ቋሚ የሥራ ዕድል | 15 | 20 | 20 | |
| 1.2 | ጊዜያዊ የሥራ ዕድል | 5 | 5 | 5 | |
| **2** | **የሀብት መጠን** | **30** | **35** | **35** | የተረጋጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተረጋገጠ የሀብትና ዕዳ መግለጫ |
| 2.1 | ጠቅላለ የሀብት መጠን | 15 | 15 | 20 | |
| 2.2 | በብድር ከተገኘው ገንዘብ ለቋሚ ንብረት የዋለ መጠን | 15 | 20 | 15 | |
| **3** | **ትርፋማነት** | **15** | **10** | **10** | • የትርፍና ኪሰራ መግለጫ<br>• የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተረጋገጠ የሀብትና ዕዳ መግለጫ |
| 3.1 | ተከታታይና ተመጣጣኝ ትርፍ ማስመዝገብ | 5 | 3 | 5 | |
| 3.2 | ከተገኘው ትርፍ ሥራውን ለማስፋት እና ወይም ለቁጠባ የዋለ ገንዘብ መጠን | 10 | 7 | 5 | |
| **4** | **የገበያ መጠን** | **8** | **8** | **10** | |
| 4.1 | ዓመታዊ የሽያጭ መጠን | 2 | 2 | 3 | የሽያጭ መረጃ በማየት |
| 4.2 | ከመንግስት ውጪ የተፈጠረ የገበያ ትስስር መጠን | 2 | 3 | 2 | የሽያጭ መረጃ በማየት |
| 4.3 | በንዑስ ኮንትራት ለሌሎች ኢንተርፕራይዞች በዓመት የፈጠረው የገበያ ትስስር ብዛት | 2 | 1 | 3 | ውል በማየት |
| 4.4 | ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች | 1 | 1 | 1 | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 4.5 | የኤግዚቪሽንና ባዛር ተሳትፎ ብዛት | 1 | 1 | 1 | በተሳትፎ የምስክር ወረቀት |
| **5** | **ምርታማነት** | **7** | **4** | **5** | |
| 5.1 | ካለው ሙሉ የማምረት አቅም የተጠቀመው | 3 | 2 | 3 | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ውጤት |
| 5.2 | የብቃት ማረጋጫ | 4 | 2 | 2 | የምስክር ወረቀት |
| **6** | **በመንግስታዊ ድጋፎች አጠቃቀም** | **6** | **5** | **5** | በአንድ ማዕከል አገልግሎት ሰራተኞች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| **7** | **የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም** | **5** | **5** | **5** | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| **8** | **ተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት** | **5** | **4** | **3** | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| **9** | **ግዴታን ስለመወጣት** | **4** | **4** | **2** | |
| 9.1 | ዓመታዊ የገቢ ግብር መክፈል | 2 | 3 | 1 | የገቢ ግብር ክሊራንስ |
| 9.2 | የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ማሳደስ | 2 | 1 | 1 | የታደሰ የምዝገባና የንግድ ፈቃድ |
| | **ድምር** | **100%** | **100%** | **100%** | |

**ማስታወሻ፡-**

(1ኛ) የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር የሚፈፀመው ለየዕድገት ደረጃው በድምር በመቶኛ/%/ ከተቀመጠው ወደ ታዳጊ $\geq$ 75% ሲያገኙ& ወደ መብቃት $\geq$ 80% ሲያገኙ& እና ወደ ታዳጊ መካከለኛ $\geq$ 85% ሲያገኙ ይሆናል::

(2ኛ) ከላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን ከከፍተኛው ነጥብ ቀጥሎ ወደታች የሚገኝ የነጥብ ውጤት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ ስሌት በመስራት ይቀመጣል::

(3ኛ) የመንግስታዊ ድጋፎች ተጠቃሚ ያልሆነ ኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃ ሽግግር ወቅት ለዚህ የተቀመጠውን ሙሉ ነጥብ ያገኛል::

አባሪ. 2

| የኢንተርፕራይዙ ዓይነት | የተሰማራበት ዘርፍ | የኢንተርፕራይዙ ሃብት መጠን | ገና ከጅምሩ ኢንተርፕራይዙ የሚፈረጀረበት የዕድገት ደረጃ | በሌሎች መመዘኛ መስፈርቶች ተመዝኖ ኢንተርፕራይዙ ከመቶ ያገኘው ነጥብ | ለኢንተርፕራይዙ የሚሰጠው የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ | አገልግሎት | እሰከ ብር 40,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 40,001 እስከ ብር 50,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | 85% እና በላይ | መብቃት |
| | ኢንዱስትሪ | ከብር 50,000 እስከ 75,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 75,001 እስከ 100,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | 85% እና በላይ | መብቃት |
| አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ | አገልግሎት | ከብር 50,000 እሰከ ብር 200,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 200,001 እሰከ ብር 500,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | ከ 85% በላይ | መብቃት |
| | | ከብር 500,000 በላይ | ታዳጊ መካከለኛ | ከ 85% በታች | መብቃት |
| | | | | 85% እና በላይ | ታዳጊ መካከለኛ |
| | ኢንዱስትሪ | ከብር 100,000 እስከ 500,000 | ታዳጊ | ከ 75% በታች | ጀማሪ |
| | | | | ከ 75% በላይ | ታዳጊ |
| | | ከብር 500,001 እስከ 1,500,000 | መብቃት | ከ 85% በታች | ታዳጊ |
| | | | | ከ 85% በላይ | መብቃት |
| | | ከብር 1.5 ሚልዮን በላይ | ታዳጊ መካከለኛ | 85% እና በታች | መብቃት |
| | | | | 85% እና በላይ | ታዳጊ መካከለኛ |